# የኛ ነገር

ወፌቱ ጎጆ ቀልሣ፣
ሥትበር ማሣ ለማሣ፣
ባሣር በቀየሰቻት በጎጆዋ እንቁላል ጥላ፣
ትውልድ ትቀጥላለች ጫጩቶቿን ፈልፍላ፣
ከአይን እስክትሰወር እልም ጭልጥ እያለች፣
በራ በራ በአፏ ለቅማ ለትውልድ ታስረክባለች፡፡
        የሰው ልጅ ግን፣
        የሰው ልጅ ግን ሰውን ሲያማ ባፍ ያጠፋል፣
        ባፉ ክቦ ባፍ ይንዳል፣
        ባፉ ይነድፋል ባፍ ይቀጥፋል፡፡
        የሰው ነገር! .... የኛ ነገር!

እርስ በርስ ስንፈራራ የጎሪጥ እየተያየን፣
ኡደቱን ሣይስት አበቅቴው የእድሜ ሲሶውን ቢነጥቀን፣
ዞር ብለን ብናሰላው ከታሪክ ማህደራችን፣
በዘመን ለፍተን የተውነውን፣
የወጣን የወረድነውን፣
የጣርን የቧጠጥነውን፣
ደክመን ሰርተን የተውነውን፣
ታሪክን እማኛ አድርጎ ታሪክ ራሱ ሲፋረደን፣
በምፀት ያስተውለናል ከታሪክ መማር ሲሳነን፡፡

        ለካስ ሃቅ ከገመድ ይሰላል እንደትንታ ድንገት ያንቃል፣
        ከቀለም ይዛመድና ብራና ታሪክ ይከትባል፣
        ህሊና ያልሣለው ብዕር በባዶው ልብን ያደማል፣
        ጅል ሽልል ያሉት ዕለት እንደበሬ ይበረያል፣
        ቀን ብሎት የሸለለዕለት የራስ ወገን ያደባያል፣
        ሞኝ የተሾመ እለት የትውልድ ተሰፋ ያመክናል፣
        ትውልድን ተስፋ ሲያስቆርጥ በዛውም ሃገር ይገላል፡፡
                የኛ ነገር ......

የጭብጡ መቋጠሪያ ውል ምን ከደማችን ቢተሣሰር፣
ኢትዮጵያዊነት ውርስ ሆኖ ሲያስተዛዝበን በግብር፣
የተስፋ እምነት ስንቅን ለእውነት ብቻ እንዳናድር፣
ተዝካር እንደለመደ ደብተራ ደርሶ ቀዳሽ ለፍትሃት ብር፣
ውሉ እየጠፋ ግራ አጋባን እንደሰነፍ ሸማኔ ድር ።
                የኛ ነገር !!..... .......

        ሃሣብ ላሣብ አልቃኝ ሲል የዜማው ድርድር ይፈርሣል፣
        በቆዳ በመወጠሩ ክራሩም አንጀት ይቆርጣል፣
        ሰሚ በሌለበት ቤት ሁሉም ቢጮህ ምን ያደርጋል፣
        የት ይደርሳል?.... .... ማን ይሰማል?..... .......
        ይልቅስ ....

ይልቅስ፡-እኛ በእኛ ልብ ገዝተን ጥርጊያውን ባናመቻች ባንተልም፣
        ቋጠሮው እየተፈታ ውል አልባ ቢሆን የኛው ህልም፣
        ግርዶሹን መግለጥ ተስኖን የልጆቻችን ህልም ሳይጨልም፣
        ቆም ብሎ ካድማስ ማዶ ነገን ማለም ሰው አይገልም
        አለዚያ ግን እንኳን ለፍርድ ለንሰሃም አንመችም፡፡

እምለዓሉ ፍሰሃ
ጀኔቫ፡ 09.01.2010
የኢትዮጵውያን ማህበር በስዊዘርላንድ (ኢማስ)
ወ/ት ብርቱካንና ሌሎች በወያኔ እስር ቤት ውስጥ የሚማቅቁ
የህሊና እስረኞችን ለማሰብ ባዘጋጀው የሻማ ማብራትና የውይይት
ስብሰባ ላይ የቀረበ ።

# የክራር ንዝረት

ክራር ከራ ከራ፣
ከጅማቷ ጋራ፣
ልቤን እየነሳች እየነዘረችኝ ፡፣
እዚህ ተቀምጬ በትዝታ አስጋልባ እዛ አደረሰችኝ፣
ሠው ሁሉ ሊቃኘው ሲወጥር ክራሩን፣
አንቺሆዬ አንባሰል ባቲን ሲያቀነቅን፡
ሳያውቁበት ቀርተው አደራደሩን፣
ብርቱካኔ ሲሉ ቅኝት አፈረሱ የትዝታውን፣
ገና ሲደረደር ልብ የሚነዝረውን የሚሰልበውን ።

ላጥር እንዳልነበር ሽቦ ለማሰር፣
ድምፅ ያደምቃል ተብሎ ቢቃኝ ከክራር፣
ጣዕም ለዛው ጠፋን ወይ መደናቀር ።

በጣት ሲነካኩት ሲፈታትሉት፣
ልብን የሚያማልል አብረው ሲያዜሙት፣
ቢገኝ አንጀት ነበር ከጠፋም ጅማት፣
የፊቱ አልሆን ሲለን መሰስ የኋሊት፣
ሰው ከሰው ተፈጥሮ አወይ ሰው ማጣት ።

እምለዓሉ ፍሰሃ
ጀኔቫ ፡ 09.01.2010
የኢትዮጵውያን ማህበር በስዊዘርላንድ (ኢማስ)
ወ/ት ብርቱካንና ሌሎች በወያኔ እስር ቤት ውስጥ የሚማቀቁ
የህሊና እስረኞችን ለማሰብ ባዘጋጀው የሻማ ማብራትና የውይይት
ስብሰባ ላይ የቀረበ ።